# ዘግይቶ ሰሚ ያገኘው እና የወቅቱ የመንግስት ጥያቄ የሆነው "የመልካም አስተዳደር" ችግር

Wednesday, 11 November 2015 13:39

-

በይርጋ አበበ

ከሁለት ሳምንታት ባልበለጠ ጊዜ ብቸኛው የአገሪቱ ባለምስል የመገናኛ ብዙሃን (የኢትዮጵያ ብሮድካስትንግ ኮርፖሬሽን) ከዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ጋር በመተባበር አንድ ዘጋቢ ፊልም አሳይቶ ነበር። በብሮድካስት ኮርፖሬሽኑ የተመለከትነው ፊልም የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የፖሊሲ ጥናት ክፍል ከሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር በመልካም አስተዳደር ላይ ባስጠናው ጥናት ዙሪያ የኢህአዴግ ጉምቱ ባለስልጣናት ወይም በተለምዶ ስራ አስፈጻሚ እና ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በመልካም አስተዳደር ላይ ያደረጉትን ውይይት ነበር። በውይይቱ ወቅትም ከአቶ መለስ ህልፈተ ህይዎት በኋላ የጠቅላይነቱን መንበር የተረከቡት አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ መንግስታቸው በመልካም አስተዳደር ችግር እየተሰቃየ መሆኑንና ህዝቡም በመንግስታቸው ላይ እምነት እያጣ እየሄደ መሆኑን ተናገሩ። እምነቱን ከኢህአዴግ ላይ እያነሳ ያለውን ህዝብም ተመልሶ እምነቱን እንዲሰጣቸው በቀጣዮቹ ስድስት ወራት ተስፋ ሰጭ ስራ ሰርተን ማሳየት አለብን ሲሉ ተናግረዋል።

ለመሆኑ መልካም አስተዳደር ምንድን ነው? የመልካም አስተዳደር መገለጫዎችስ ምንድን ናቸው? መልካም አስተዳደር በሰፈነባቸውና በተዳፈነባቸው አገራት መካከል ያለው ልዩነትስ ምንድን ነው? የመልካም አስተዳደር ባህል በኢትዮጵያ በተለይም በኢህአዴግ የስልጣን ዘመን ምን ይመስላል? የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ከዚህ በታች አቅርበናቸዋል። ጉዳዩን እንዲያጠናክሩልን የተለያዩ ዓለም አቀፍ እና የአገር ቤት ሰነዶችን ያገላበጥን ሲሆን የፖለቲካ ምሁራንንም ለማነጋገር ሞክረናል።

## መልካም አስተዳደር ምንድን ነው?

በመጀመሪያ በርዕሰ ጉዳዩ እና በይዘቱ ላይ መስማማት መድረስ አለብን ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም ባለፉት ሁለት ወራት ኢህአዴግ የመልካም አስተዳደር ችግር አለብኝ ብሎ በይፋ ሲናገር በሌላ በኩል ደግሞ ትንሽ ቀደም ባሉት ወራት በተለይም ከምርጫ 2007 በፊት የመልካም አስተዳደር ችግር ሲያልፍም አይነካኝ ብሎ የተናገረ ፓርቲ ነው። ይህ የኢህአዴግ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ አነጋገር መልካም አስተዳደር በወራት ልዩነቱ አሰራሩ እና ትርጉሙ ይለያያል እንዴ? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ለዚህ ጥያቄ መልስ እንዲሆነን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽን ቢሮ ያወጣውን ሪፖርት ለዋቢነት እንጠቀማለን።

የድርጅቱ ሰነድ "መልካም አስተዳደር እና ሰብአዊ መብት" በሚለው ዘውግ ስር "It has been said that good governance is the process whereby public institutions conduct public affairs, manage public resources and guarantee the realization of human rights in a manner especially free of abuse and corruption, and with due regard for the rule of law." ሲል ያስቀምጣል። የሀሳቡን ትርጓሜ ወደ አገርኛ ለመመለስ ስንሞክር "መልካም አስተዳደር የህዝብ ጉዳዮችን፣ የህዝብ ሀብትን የማስተዳደርና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ዋስትና መስጠት በተለይም ህዝብን ከመበደልና ከሙስና ነጻ የሆነ አስተዳደር በማስፈን የህግ የበላይነትን የማስከበር ሂደት ነው" የሚል ይሆናል።

በሌላ በኩል ደግሞ ዊኪ ፔዴያ የተባለው ድረ ገጽ መልካም አስተዳደርን ሲገልጸው "መልካም አስተዳደር የሰብአዊ መብቶችን ሙሉ በሙሉ ማክበር፣ የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ ውጤታማ የሆነ አሳታፊነት የተላበሰ የፖለቲካ ብዝሃነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን የተላበሱ ተቋማትን ማስፈን፣ የህዝቡን ፖለቲካዊ አቅም ማጎልበት፣ የህዝብን የንብረት ባለቤትነት

ማረጋገጥ እና ሀላፊነትን፣ መቻቻልን እና በአንድ የሚያግባባ ነጥብ ላይ (በተለይ በፖለቲካ አመለካከት የሚታገሉ ድርጅቶች) ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን ፈቃድ መስጠት የሚያስችል ምቹ መደላድላዊ ሜዳ መፍጠር ነው" ይላል።

በሁለቱ ሰነዶች ማብራሪያ በመመርኮዝ "መልካም አስተዳደር ማለት ይህ ነው" የሚል ድምዳሜ ላይ ልንደርስ እንችላለን።መልካም አስተዳደር ይህ ከሆነ ኢህአዴግን ለህልውናዬ ሳይቀር አደጋ ሆኖብኛል ያለው ለምንድን ነው? የትኞቹ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ናቸው ለኢህአዴግ ፈተና የሆኑበት? ለሚሉት ጥያቄዎች ደግሞ በቀጣዩ ንዑስ ርዕስ እንመለከታለን።

## መልካም አስተዳደር በኢትዮጵያ በተለይም በዘመነ ኢህአዴግ

ኢህአዴግ ለ 17 ዓመታት እልህ አስጨራሽ የጫካ ትግል አድርጎ ወታደራዊውን የደርግ መንግስት ድል ከነሳ በኋላ ስልጣኑን እንደጨበጠ በኢትዮጵያ ሬዲዮ በኩል መልዕክት በማስነገር ነበር የአገሪቱ ገዥ መሆኑን ያወጀው። በወቅቱ የፓርቲውን መልዕክት ያቀረቡት አንድ ታጋይ "ደርግ ሲጠቀምበት የነበረውን ሬዲዮ ጣቢያ ብሶት የወለደው የኢህአዴግ ሰራዊት ተቆጣጥሮታል" በማለት ነበር። ብሶት የሚለው ቃል በራሱ ምንድን ነው? ብሶት የወለደው ማለት ምን ማለት ነው? ኢህአዴግን ብሶት የወለደውስ በምን መልኩ ነው?

በአብዛኛው ኅብረተሰብ ዘንድ ብሶት የሚለው ቃል ትርጉሙ በአስተዳደር የሚፈጸም ከመጠን ያለፈ በደል እና ግፍ የሚል ትርጓሜ ይኖረዋል። ኢህአዴግ ብሶት የወለደው በምን መልኩ ነው? ለሚለው ጥያቄ ደግሞ፤ የአጼ ኃይለሥላሴ መንግስት በዘውዳዊ መንግስታቸው ባሰፈኑት የቡርጂ መደብ እና የወታደራዊው የደርግ መንግስት ደግሞ በአገሪቱ በዘረጋው አምባገነናዊ አስተዳደር ምክንያት አገር እና ህዝብ ለከፍተኛ በደልና ግፍ ሲዳረጉ ነው ኢህአዴግ የተወለደው። ኢህአዴግም ይህንን ብሶት ለመሻር ከፍተኛ እና የመቶ ሺህዎችን ሰማዕታት ህይወት ያስከፈለ ትግል አካሂዶ የአገሪቱን ርዕሰ መዲና ከተቆጣጠረ በኋላ ነው "ብሶት የወለደው የኢህአዴግ ሰራዊት ...." ያለው። ያ ብሶት አሁንስ የት ሄደ? አለ ወይስ መልኩንና ቅርጹን ቀይሮ እየኖረ ነው? የሚሉት ጥያቄዎች ወሳኝ ናቸው።

የቀድሞው የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ዳንኤል ተፈራ በዚህ ጉዳይ ላቀረብንላቸው ጥያቄ ሲመልሱ "መልካም አስተዳደር እኮ ከስርዓት ጋር የሚያያዝ ነው። ይህ ማለት አሁን ያለው ስርዓት በዴሞክራሲ ሽፋን የተመሰለ እንጂ ራሱ ዴሞክራት ስላልሆነ መልካም አስተዳደር አለ ማለት አይቻልም። የቀደመው የህዝብ ብሶት አሁንም አለ" ሲሉ ይናገራሉ። ኢህአዴግ በበኩሉ ስልጣን በጨበጠባቸው ባለፉት ዓመታት የዘመናትን የህዝብ ዴሞክራሲያዊና የልማት ጥያቄዎች በበቂ ሁኔታ መቅረፍ እንደቻለ ይናገራል።ሆኖም ግን ፓርቲው ሰሞኑን በግልጽ ከማመኑ በፊትም ቢሆን በመልካም አስተዳደር እና በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታው መጠነኛ መዳከም አለብኝ ብሎ ተናግሯል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የመልካም አስተዳደር እውነተኛ ጣዕም የሚታወቀው "የሲቪል፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ መብቶች ዋስትና ሲያገኙ ነው" ያለ ሲሆን አያይዞም "ትልቁ ጥያቄ ግን በአገሪቱ ያሉ የዴሞክራሲ ተቋማት የጤና፣ የመኖሪያ ቤት ባለቤትነትን፣ በቂ የምግብ አቅርቦት፣ ጥራት ያለው ትምህርት የማቅረብ እና ፍትሃዊ የሆነ የፍትህ ስርዓት እና የግለሰባዊ ዋስትና ተረጋግጠዋል ወይ የሚሉት ናቸው" በማለት ይደነግጋል።

በርካቶች በዚህ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መመዘኛ በተለይም በፍትህ ስርዓቱ እና በትምህርት ጥራት እንዲሁም በግለሰባዊ ዋስትና እና በቂ ምግብ ለዜጎቹ በማቅረብ በኩል የኢህአዴግ መንግስት አሁንም ገና ያልሰራው ትልቅ የቤት ስራ ከፊቱ እንደተቀመጠ ነው ሲሉ ይናገራሉ። በዜጎች የመኖሪያ ቤት አቅርቦት በኩልም ቢሆን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የመኖሪያ ቤት የሌላቸው መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ መንግስት የሚከተለው የመሬት ፖሊሲ እና የዜጎች የመግዛት አቅም ዝቅተኛ መሆን ነው ሲሉ ይናገራሉ። ትምህርትን በተመለከተ በቅርቡ መቀሌ ላይ ተካሂዶ በነበረው የውይይት መድረክ

ላይ የትምህርት ሚኒስትሩ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ የአገሪቱ የትምህርት ጥራት በከፋ ደረጃ አደጋ ላይ ነው ባይባልም የጥራት ጉድለት እንዳለበት ግን መንግስታቸው እንደሚያምን ተናግረው ነበር።

የቀድሞው የኢዴፓ ሊቀመንበር አቶ ልደቱ አያሌው ግን "ኢህአዴግ ላለፉት የስልጣን ዘመኑ ካሳካቸው አብይ ስራዎች መካከል ከእነ ድክመቶቻቸውም ቢሆን የልማት ስራዎቹ ናቸው። የትምህርት ሽፋንም ሆነ በጤና በኩል እና የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ላይ ካለፉት ስርዓቶች በተሻለ ማድረስ ችሏል" ሲሉ ይናገራሉ።

ለመሆኑ የመልካም አስተዳደር ችግር ለኢህአዴግ ፈታኝ የሆነው በምን መልኩ ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ እንዲሰጡን የጠየቅናቸው አቶ ልደቱ "በቴሌቪዥን የተካሄደውን የጥናት ሪፖርት አይተህ ከሆነ ከችግሩ ምንጭነት ይልቅ ትኩረት ያደረገው ስለ መፍትሔው ነበር። በመጀመሪያ መታየት ያለበት ይህ ስርዓት በመልካም አስተዳደር ችግር እንዴት ሊዘፈቅ ቻለ? የሚለው ነጥብ ነበር" ይላሉ። አቶ ልደቱ አያሌው አያይዘውም "ይህ መንግስት (ኢህአዴግ) መልካም አስተዳደርን የሚገልጸው በልማት ስራ እና በቢሮክራሲው የሚሰጠውን አገልግሎት ብቻ ነው። በዚህም የተነሳ በተደጋጋሚ ጊዜ የሚገልጸው መልካም አስተዳደርን ከቢሮክራሲው ጋር እያያያዘ ነው። ነገር ግን መልካም አስተዳደር ቢሮክራሲ ወይም ልማት ላይ ብቻ ሳይሆን በሰብአዊ መብት እና በዴሞክራሲ ግንባታው ላይም ትኩረት ያደርጋል" ይላሉ።

"ለመልካም አስተዳደር ችግር ምክንያቱን አይቶ መፍትሔ መስጠት ካልቻለ ለህልውናው አደጋ መሆኑን ይናገራሉ። መንግስት ካድሬዎችን በስራ ኃላፊነት የሚያስቀምጠው በግለሰቦቹ የትምህርት እና የስራ ልምድ ላይ ተመርኩዞ ሳይሆን በፓርቲ አባልነታቸው ባላቸው ታማኝነት ላይ ብቻ በመሆኑ በራሱ የማይተማመን እና ኪራይ ሰብሳቢ ካድሬ አፍርቷል። ይህ ደግሞ ለስርዓቱ አደጋ ነው" ብለዋል።

የቀድሞው የአንድነት የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ዳንኤልም "የስርዓቱ ፈታኝ ሆኖ የቀረበው የመልካም አስተዳደር ችግር ምክንያቱ በአባላት ምልመላ ነው። አሁን እኮ በግልጽ "አንተ ግን ለምን የኢህአዴግ አባል ሆነህ አትጠቀምም?" ብለው የሚናገሩ ሰዎች በዝተዋል። በዚህ ደረጃ ትዝብት ላይ የወደቀ ስርዓት ስጋቱ የራሱ አካሄድ ነው" ይላሉ።

## መልካም አስተዳደርን ማስፈን እንዴት?

አቶ ኃይለማሪያም በቴሌቪዥን በተላለፈውና ከወትሯቸው በተለየ መልኩ ትኩረት ሰጥተው እና ኮስተር ብለው ሲናገሩ በታዩበት ንግግራቸው "እስከመቼ የመልካም አስተዳደር ችግር አለ ብዬ አወራለሁ? ሁላችንስ እስከ መቼ የመልካም አስተዳደር ችግር አለ ብለን እናወራለን" ብለው ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ከዚህ በፊት የመልካም አስተዳደር ችግር አለ፣ የመሬት ችግር አለ፣ ጨረታ ላይ ችግር አለ፣ ገቢዎችና ጉምሩክ ላይ ችግር አለ፤ ከሚባለው አልፈን እውነት ምንድን ነው ያለው? የሚለውን መፈተሽ አለብን። በጥናቱ የቀረቡትን ችግሮች ከልብ መቀበል ይገባል" በማለት የመልካም አስተዳደርን ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ መደረግ ስላለበት አካሄድ ተናግረዋል። ለዚህም በንቅናቄ መልኩ ዘመቻ መክፈትና አመራሩ ቁርጠኛ ሆኖ መንቀሳቀስ እንዳለበት ተናግረዋል።

ሌሎች ከኢህአዴግ በተጓዳኝ ያሉ የፖለቲካ ልሂቃን ግን ከዚህ ሀሳብ ጋር አይስማሙም። ካነጋገርናቸው ገሚሶቹ "የመልካም አስተዳደርን ችግር በዘመቻ መቅረፍ አይቻልም።በመጀመሪያ ፓርቲው ራሱን መፈተሽ አለበት። የመገናኛ ብዙሃን ነጻነት ሳይከበር፣ ነጻ እና ገለልተኛ መገናኛ ብዙሃን ሳይኖሩ፣ የዴሞክራሲ ተቋማት ከአንድ ፓርቲ አገልጋይነት ሳይላቀቁና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሳይገነባ ዝም ብሎ የመልካም አስተዳደርን ችግር በዘመቻ እቀርፋለሁ ማለት ፓርቲው የለመደውን ማደናገሪያ አካሄድ በድጋሚ ተናገረ ብለን ከመግለጽ ውጭ ሌላ ማለት አይቻልም" ይላሉ።

የአቶ ኃይማሪያምን ሀሳብ ከሚቃወሙት መካከል አንዱ የሆኑት አቶ ዳንኤል ተፈራ "የመልካም አስተዳደርን ችግር በመፈክር ወይም የአንድ ሳምንት አጀንዳ አድርጎ በመንቀሳቀስ ሊቀረፍ የሚችል ችግር አይደለም። ችግሩን ለመቅረፍ የሚደረገው

ጥረት መጀመር ያለበት አባላትን ከመመልመል ላይ ነው። ህዝብን እና አገርን ለማገልገል ቆርጠው የተነሱ እና በዓላማ የሚንቀሳቀሱ አባላትን መመልመል እንጂ ለፓርቲ ባላቸው ታማኝነት ብቻ አባላትን እየመለመለ ያለ መንግስት የመልካም አስተዳደርን ችግር በቀላሉ ይቀርፋል ብዬ መናገር ይከብደኛል" ይላሉ። አቶ ዳንኤል አያይዘውም "ስርዓቱ ቀደም ብሎ ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ነበሩ። በመጀመሪያ ዴሞክራሲን ማስፈን ነበረበት። በአጠቃላይ ግን ስርዓቱ አካሄዱን እስካላስተካከለ በተለይም በዴሞክራሲ ግንባታ ላይ ካልሰራ ለውጥ ያመጣል ብዬ ማሰብ ይከብደኛል" ብለዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ አነጋገርም ተገቢውን መልስ አግኝቶ የመልካም አስተዳደር ችግር ተቀርፎ የህዝብ ጥያቄ ይመለሳል ብለው እንደማያምኑ የሚናገሩት አቶ ዳንኤል፤ "የአቶ ኃይለማሪያም ንግግር ከፕሮፓጋንዳነት ያለፈ ተጨባጭ ለውጥ ያመጣል ማለት አይቻልም" ሲሉ ይናገራሉ። አቶ ዳንኤል ምክንያታቸውን ሲያቀርቡም "የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታንም ሆነ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ትልቁ መሳሪያ ሚዲያ ነው። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ግን ከ 90 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ባለበት አገር በሳምንት ሶስት ወይም አራት ጋዜጦች ብቻ እየታተሙ ነው ያሉት። አጠቃላይ በነጻው ፕሬስ ላይ ያለው ሂደት የሚያበረታታ እና ተስፋ ሰጭ አይደለም። በማህበራዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ጠንካራ ሂስ የሚያቀርብ ሚዲያ በሌለበት አገር መልካም አስተዳደርን ማስፈን የሚታሰብ አይደለም" በማለት ተናግረዋል።

የኢዴፓ የቀድሞ ሊቀመንበር አቶ ልደቱ አያሌው ደግሞ "መልካም አስተዳደር ከዴሞክራሲ ስርዓት ተለይቶ የሚታይ ነገር አይደለም። ስለመልካም አስተዳደር ስትናገር የዴሞክራሲ ግንባታን አብሮ ማስኬድ የሚለውንም ታሳቢ ማድረግ አለብህ። ወይም በሌላ አገላለጽ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ያላጎለበተ የመልካም አስተዳደር ችግርን መፍታት አይቻልም" ይላሉ።

የመልካም አስተዳደር ችግር ለዓመታት ሲንከባለል ቆይቶ መንግሥት አሁን መስማት ጀምሯል። መስማቱ ብቻ ሳይሆን ቶሎ መልስ መስጠትና ችግሩን ከስሩ ማድረቅ ደግሞ ቀጣይ ሥራ ነው። ለዚህ ደግሞ ትልቁን ኃላፊነት የሚወስደው መንግሥት ነው። ■

ስንደቅ